# ተባበር

## ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

“አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
“ነገራችን ሁሉ የ'ምባይ ካብ÷ የ'ምባይ ካብ።”
ቀኛ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ

እሱ ነው ያጠፋው ብሎ ሲወናጀል
ጣቱንም ቀስሮ እስበስ ሲጠቋቆም
በቡድን ተከፍሎ ለቡድኑ ሲቆም
እኮ ታዲያ ማነው ለኢትዮጵያ የሚቆም?

እሷማ ተረስታ
ጠብ ሁኖ በሌላ
ሃኪሙ ደጋ ነው÷
ታማሚው እቆላ!

ኢሳማው እዚህ
ጥይቱ ማዶ
ዣንጥላው እዚህ
ዶፍ እዛ ወርዶ።

የኛማ ነገር
ለሠሚው ግራ÷ የወለፈንዲያ
አንደኛው ወዲህ
ሌላኛው ወዲያ!

ተኳሹ እዚህ
አውሬው ወዲያ እንዲያ
የኛማ ነገር
ያሰኛል 'ኤጭ! ወዲያ!'

አንዱ የእንቶኔ
ሌላው የ'ገሌ
አንዱ የ'ከሊት
ሁሉም የየግሌ።

አንዱ ላንዱ ሲቆም
ብሎት እሱን የኛው
ለኢትዮጵያ እሚቆም
ታዲያ የትኛው?

“አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
“ነገራችን ሁሉ÷ የ'ምባይ ካብ የ'ምባይ ካብ።”

ሰይፍ በሌለበት
ኀያል ሆኖ ድጉስ
ዙፋን በሌለበት
ሁሉ ሆነ ንጉሥ::

የነጋሲው ብዛት
መቼ ይቆጠራል
ሁለም በብብቱ
ዘውድ ይዞ ይዞራል::

ሁለት አንበሶች ሥጋውን ረስተው
ሲቆሳሰሉ÷ ሲበጫጨቁ ነገር ከረረ÷
ባይኖር ጠባቂ÷ሥጋውን ነጥቆ
ጮሌው ጨሉሌ ይዞ በረረ!

ፍየሉ ውዲህ
ቅዝምዝም ወዲያ
አንት ለሱ ስትቆም÷ ሌላው ሲቆም ለዚያ÷
ማን ይቁምላት ለኢትዮጵያ ታዲያ?

ትላለህ አንተ “እኔ ነኝ ትክክል!”
እሱም ይልሃል “እኔ ነኝ ትክክል!”
ሁሉም ሲታገል አያጣም እክል÷
ምናልባት ናችሁ ሁላችሁ ትክክል፤
ወይም ስህተተኞች ስትሉ ነን ልክ::
ለኢትዮጵያ ስትል ይህን ችላ ብለህ
ተቻቻል÷ ተባበር÷ አያዋጣም እልክ::

ቁጭ ብለህ ተወያይ
አታጣም መፍትሄ÷
በየፊና መጓዝ
አያዋጣም ይሄ::

ተኳሹ እዚህ
ኢላማው ማዶ÷
ዣንጥላው እዚህ
ዶፍ እዛ ወርዶ::
ፍየሉ ወዲህ
ቅዝምዝም ወዲያ
ወገን ወግነህ ስትቆም ለራስህ÷
ማን ይቁምላት ለኢትዮጵያ ታዲያ?

የሚቆምላት አታጣም ባገር
“ያለኔ ማን!” ብለህ አትንቀባረር÷
ይፈልቃል መሪ
አንት ብትባረር::

EthioLion.Com

ራስህን ዝቅ አርገህ
ይቅርታ ጠይቅ በትህትና፥
ትሁትስ ሆነህ ልብህ ቢቀና
ትምርሃለች እናት ናትና።

አሻፈረኝ ብለህ ሸር ሸርበህ
በእናትህ ላይ ብታምጽ በ'ብሪት፥
ቤንዚን አርከፍክፈህ ለራስህ መጥፊያ፥
ተረዳ ራስህ ላይ እንደጫርክ ክብሪት።
ራስህን ብታውል
ከኢትዮጵያ በላይ
እወቅ መሥመጥህን
እውርደት ቀላይ!

እሥበሱ ሲፋጅ፥ ፎክሮ፥ ብሎ
“ሁሉን ቀድሜ እኔ እላይ ልውጣ!”
ከትክት ብላ ሳቀች
እላይ ሆና ጠጣ።

ፍጻሜ ያጣ
የጦቢያ ፍዳ
እዳ ከፍላ ሳያልቅ
ልትገባ ሌላ እዳ?

ጦርነት ሳያከትም
አዲስ ጦርነት?
ሃርነት ሳይኖር
አዲስ ባርነት?

ሊጡ ሳይቦካ
ወጡ ሳይቁላላ
እመሶብ ቂብ አለ
በላተኛው ሁላ!

ኢትዮጵያን ሊቤዧት መሥሎኝ ነበር ገሩ
ከወደኋላው ነው ጅራትና ጉዱ፥
ሃቁ ፍንትው አለ–
ሊቀራመቷት ነው፥ ለካስ ሸር ጉዱ!

ገድዋ የገደደ ያልታደለች እናት
ወልዳ፥አሳድጋ እንኳንስ ሊጦሯት
ጥርስ ይስላሉ ደሞ በተራቸው
ትራፊዋን ግጠው በአፅሟ ሊያስቀሯት።

“ከትብስ” “ትሻል”ን እስቲ ልሞክራት
ብላ'ንጂ ኢትዮጵያ ይዟትም እልክም
“ያላንተ ሰው የለም፤”
በማለት ኢትዮጵያ አንተን አታመልክም።

EthioLion.Com

አሿት ድብቅ ልጆች-
የውጪ ነፍሥ ግቢ÷ ከባሰስ ጨኸትዋ
ብቅ ብቅ የሚሉ÷
በእመርታ ወጥተው ከስውር ብብትዋ::

እራስህን አርቅ!
ስህተትህን አርም!
አንቅራ እንዳትተፋህ
ኢትዮጵያ ብላህ እርም!

አብረህ ጀመርከው
ጨርሰው አብረህ፤
ተው አትለያይ
ቀጥል ተባብረህ::

ያንተን ፍላጎት
ወደ ጎን ትተህ
የጦቢያን ጥቅም ቅድሚያውን ሰጥተህ
ይቅር ተባባል ጥላቻን ገትተህ::

ተው ለኢትዮጵያ ቁም፤
አትቁም ለጎራህ!
ስትተባበር ነው
ሌላው የሚፈራህ::

ተባበር÷ አንድ ሁን
የግልህን ትተህ
ተቻቻል ላላማህ
ልዩነትህን ገትተህ::

“አገሬ ተባብራ
ካልረገጠች ርካብ
ነገራችን ሁሉ
የ'ምቧይ ካብ፤ የ'ምቧይ ካብ!”

ከሳንፍራንሲስኮ ወደ ዲሲ ስበር የኢትዮጵያ ጉዳይና በፖለቲካው ዙሪያ ያለው ትርምስ በጣም ስለ አሳዘነኝና ስለአሰጋኝ÷ የህብረትን አስፈላጊነት በገለልተኝነትና በተራ ኢትዮጵያዊነቴ ለመግለጽ አየር ላይ ሆኜ ገጠምኩት::

እኤአ መስከረም 7 ቀን 2007

EthioLion.Com

EthioLion.Com